## የእግዚአብሔርን ጥበብ በመንፈስ ቅዱስ መካፈል።

ትምህርት ሦስት:- **የእግዚአብሔርን መንፈስ ለመቀበል ምን እናድርግ?**

**ዓላማ:-**

- የእግዚአብሔርን መንፈስ የመቀበልን አስፈላጊነት በቃሉ ማረጋገጥ
- የእግዚአብሔርን መንፈስ መቀበል የሚቻልበትን መንገድ በቃሉ ማመላከት።

**መግቢያ:-** የእግዚአብሔርን ጥበብ ለመካፈል ያለ መንፈስ ቅዱስ እንደማይቻል እና ለፍጥረታዊው ሰው የእግዚአብሔርን መንፈስን ጉዳይ ሊረዳውም ሆነ ሊቀበለው እንደማይችል በቀደመው ትምህርት ተመልክተናል።ዛሬ ደግሞ የእግዚአብሔርን መንፈስ ስለመቀበል በመፀሀፍ ቅዱስ ትምህርት መሰረት እንመለከታለን።

**1: ስለኢየሱስ ማንነትና ማዳን በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ማመን።ዮሐ 3:3-18 16:7 7:37-39**

1:1 ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ማመን

1:2 በኢየሱስ አዳኝነት ብቻ ማመን።

1:3 ኢየሱስ የሰጠውን ተስፋ ማመን።

**2: እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን እንዲሰጠን በእምነት መለመን።**

2:1 በእምነት ለሚለምኑ መንፈስ ቅዱስ ይሰጣል **ሉቃ 11:13**

2:2 ያለመጠራጠር የሚለምን ይቀበላል። **ያዕ 1:6**

2:3 እግዚአብሔርን ለሚታዘዙ መንፈስ ቅዱስ ይሰጣል **ሐዋ 5:32 ዮሐ 14-15-17**

**3: በህብረት ፀሎት ያለማቋረጥ መትጋት**

3:1 በወንጌል ተልዕኮ በማህበር መፀለይ **ሐዋ 5:32**

3:2 በእውነተኛ እምነት ለመታነፅ በማህበር መፀለይ **ይሁዳ 20**

**ማጠቃለያ:-** ዛሬን ጨምሮ ለሶስት ተከታታይ ሳምንታት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት የእግዚአብሔርን ጥበብ ስለመካፈል ተምረናል።ትኩረታችንም የነበረው **የእግዚአብሔርን ጥበብ በመንፈስ ቅዱስ የመካፈልን አስፈላጊነት መገንዘብ፣መንፈሳዊው ሰውና ፍጥረታዊው ሰው ያላቸውን ልዩነት ማወቅና** ዛሬ እንደተመለከትነው **መንፈስ ቅዱስን ለመቀበል ምን ማድረግ አለብን** የሚለው እውነት አይተናል። እንግዲህ እነዚህን እውነቶች መገንዘብ እና በእምነት መለማመድ ለመንፈሳዊነታችን ወሳኝ ስለሆነ ትኩረት ልናድርግባቸው ይገባናል።